የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

የካቲት 4 ቀን 2003 ዓ.ም

## ሕዝባዊ ትግሉን ለማጨናገፍ የተጀመረው ሴራ ይከሽፋል!

በሰሜን አሜሪካና በአረብ ሀገሮች በአጠቃላይ የጀመረው ሰፊ የሕዝብ ተቃውሞና የሥርዓት ለውጥ ፍለጋ ትግል በገፍ ሲበደልና ሲሰቃይ በቆየው የኢትዮጵያ ሕዝብም ዘንድ ተቀጣጥሎ የወያኔን አገዛዝ ከሥልጣን ያሽቀነጥራል ተብሎ እየተጠበቀ ባለበት፤ ይህንንም ታሪካዊ ትግሉን ለማድረግ ኢሕአፓም የሕዝብ ወገኖችም እየጣሩ ባሉበት፤ የመለስ አገዛዝና በቀጥታ ሆነ በእጅ አዙር፤ አወቁም ሆነ በአደገኛ አላዋቂነት ይህን የሕዝብ ትግል ለማፈንና ከተነሳም በአጭር ለመቅጨት ሴራዎች እየተጎነጎኑ መሆናቸውን ኢሕአፓ እያጋለጠ ያወግዛል።

የመለስ አስተዳደር በአንድ በኩል ደሞዝ ጨምሪያለሁ፤ ኑሮ የተወደደው በነጋዴዎች የተነሳ ነውና ዋጋ ተመን ቀንሼ መድቤያለሁ፤ ለዕድገት ሰርቻለሁ፤ ...ወዘተ እያለ ድለላውን ማር አስመሰሎ ሊያስልስ ሲጥር በሌላ በኩል ልዩና ታማኝ ጦሮቹን በተጠንቀቅ አድርጎና በተለይም ወደ አዲስ አበባ እያጓጓዘ፤ በካድሬዎቹ አማካይነት ሕዝብን በየቀበሌው እያስፈራራና የምስጢር ስብሰባዎችን አድርጎ አድማና ሰልፎችን በኃይል እንዴት ማስቆም እንደሚችል ዕቅድ አውጥቶ እየተዘጋጀ ነው። ይህን የወያኔ አፍራሽ ጥረት በማገዝ ደረጃም የአሉባልታና አደናጋሪ ቅስቀሳ ቅጥረኞቹ ደግሞ ለሕዝብ የተቆረቆሩ አስመስለው ግን ወያኔ ይፈጃችኋልና አርፋችሁ መቀመጡ ይሻላል እያሉ መካሪ ሆነውና መስለው በትግል እሳት ላይ ውሀ ሊያፈሱ ላይ ታች እያሉ ናቸው። ሌሎች ደግሞ ሕዝብ በራሱ ይነሳ፤ ድርጅቶች ተነስ አትበሉት ብለውና የድርጅቶችን ወሳኝ ሚናም እየሰረዙ ያልተደራጀና ትግሉን በግብታዊነት ቢጀምርም በድርጅቶቹ ድጋፍና እንቅስቃሴ ሊጠናከር የሚገባውን ትግል ከወዲሁ ጉልበትና አቅጣጫ ለማሳጣት ተነስተዋል።

በዚህም በዚያም ገዢ ነኝ ባዩ ክፍል በጭንቅ ላይ መሆኑና የሕዝብንም ፍንዳታ ፈርቶ ተጨንቆ መገኘቱ የሚታይ ነው። ወያኔም ሆነ ማንም ጨቋኝ ሥርዓት ፍጅትን ሳይሞክር ከሥልጣን እንደማይለቅ የታወቀ ነው። ይህ ለመለስ አገዛዝ ብቻ የተሰጠው ልዩ ዕውነታ አይደለም። በግብፅና ቱኒዝያ መቶዎች ሞተዋል፤ የሁለቱም ሀገሮች የአፈናና የጦር ተቋሞች በቀላሉ የሚገመቱ አልነበሩም። ምንም እንኳን መለስ የራሱን የትግራይ መኮንኖች በከፍተኛ ደረጃ ቢመድብምና የድርጅት የሆነ ጦር ቢኖረውም በርካታው ወታደር ከሌሎች ብሄረሰቦች የተውጣጣ መሆኑም የሚታወቅ ነው። የመለስ አገዛዝ በልዩ ደረጃ የሚፈራና አይበገሬ ነው የሚባል አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብም መስዋዕትነትን ፈርቶ መብቱና ሀገሩን አሳልፎ ይሰጣል የሚሉ ደግሞ የሀገርና የሕዝብን ታሪክ የሚያወቁ አይደሉም። ስለዚህም የሕዝብ አመፅ በኢትዮጵያ ሲፈነዳ የመለስ

አገዛዝ በግድያ ይህን ለማስቀም መጣሩ--በ1997 እንደታየው--መሞከሩ አይቀርም፡፡ ለዚህ መድኃኒቱ ይገሉናል ብሎ አለመታገል፤ አለማመፅና እንደ ባርያ መገዛት ሳይሆን--ቀን ተቀን እየገደሉንና ሀገራችንንም እያዋረዱ ባሉበት-- የመጣ ቢመጣ ትግላችን ከግብ ሳይደርስ ወደ ኋላ አንመለስም ብሎ በቆራጥነት ትግልን መቀጠል ነው፡፡ እንደ ቱኒዚያና ግብፅ ሕዝብ፤ እንደ የካቲት 66!

የመለስ አገዛዝ እንዲወድቅ፤ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ፤ ሁሉን አቀፍ የሽግግር መንግሥት እንዲመሠረት፤ በሕዝብ ተሳትፎ ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግሥት ተረቆና ፀድቆ ነፃ ምርጫ እንዲካሄድ ትግሉ መነሳትና መቀጠልም አለበት፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት ሁሉ እንዲሟላ የመለስ አገዛዝ መወገድ አለበት፡፡ በመሆኑም በሀገራችን የሕዝብ አመፅ አይነሳም፤ ሊነሳ አይችልም ወይም ከተጀመረ ግድያ ይበዛልና ባይጀመር ይሻላል የሚሉ ወያኔዎች የሚፈልጉት ግብ አይሳካላቸውም፡፡ ራሳቸውን የሕዝብ ወገን የሚሉ የተደናገሩ ክፍሎች ደግሞ አውቀው ሆነው ሳያውቁ የወያኔን ማስፈራሪያ መደጋገማቸውን ማቆም አለባቸው፡፡ የካቲት 66ና የካቲት 2003 አንድ ባይሆኑም በይዘታቸው ግን ተመሳሳይነት ሊኖራቸው ይችላልና ይህን ተግባራዊና ሐቅ ለማድረግ ድርጅቶች ከሕዝብ ጎን ሆነው መጣር አለባቸው፡፡ በወጣቶች የተጀመረውና የተስፋፋውን የግብፅ ሕዝብ ትግል ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በአድማ አጅቦት ለውጤትም እያበቃው ነው፡፡ በኢትዮጵያም ተማሪው አስተማሪው፤ ሠርቶ አደሩ በሞላ ተያይዞና አንድ ሆኖ ሊነሳ ይችላል፤ መቻልም አለበት--የተጫነበትን ቀንብር አውልቆ መጣል ከፈለገ፡፡ ለአገዛዙ ተገዢ ሆኖ ያለው ጦርም ሊከፈል ሊከፋፈልና በሕዝብ ላይ ብረት አናነሳም ሊል የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር መቻሉን ባለፈው አብዮታችን አይተናል፤ በግብፅና በቱኒዚያም ያየነው ነው፡፡ የትግልና የድሉ ውጤት ግን በመሰሪዎችና ባዕድ ቅጥረኞች እንዳይቀማ ከወዲሁ ማሰብና መዘጋጀት ይኖርብናል ማለት ነው፡፡ ቀዳሚው ግን በአመፅ መነሳት ነው፡፡

የኢትዮጵያን ሕዝብ ከማመፅና ታሪክ ከመሥራት የሚያግደው ማንም ሀይል የለም፡፡
የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመብቱና ለሀገሩ መሰዋትን አይፈራም!
በጋራ እናምፅ፤ የመለስን አገዛዝ እናስወግደው!!
እናቸንፋለን!!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France